5 ኛ ክፍል

የመፀዳጃ ቤት ጥቅም

ከተላላፊ በሽታ ለመጠበቅ እንዲሁም ምቹ ጠመኖሪያ አካባቢና ጥሩ መዓዛ ያለበት አካባቢ እንዲኖር ይረዳል።

ለባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂ ለመጠቀም ሀይል ለማመንጨት ይጠቅማል ።

ሊበሰብሱ የሚችሉ ደረቅ ቆሻሻዎች ቀብሮ በማበስበስ ለአፈር ለምነት ለመጨመር እንደማዳበሪያ እንዲያገለግሉ ማድረግ ይችላል።

<u>የመፀዳጃ ቤት ንፅህና ጉድለት የሚያስከትለው ችግር</u>

1. **በሽታ አምጪ ጀርሞች በቀላሉ እንዲራቡና እንዲሰራጩ በማድረግ በጀርሞቹ አማካኝነትም በሽታ በቀላሉ እንዲስፋፋ ያደርጋሉ።**

2. **በአካባቢው የመጥፎ ሽታ ጠረን ምንጭ በመሆን በአካባቢው የሚኖሩ ሰዎች ማወከና ያአካባቢን መበከል ያስከትላሉ።**

5.2 **የምግብ ንፅህና**

የምግብ ንፅህና አጠባበቅ

የምግብ ንፅህና መጠበቅ ማለት ጤንነትን ከሚጎዱ አካላት ምግብን ነፃ ማድረግ ማለት ነው።

ምግብ ሳይበላሹ ለረጀም ጊዜ የማቆያ ዘዴዎች

1. **በጨው ማቆየት፡-** **በጨው ማሸት ወይም መዘፍዘፍ። ለምሳሌ ስጋና አሳ**

2. **በስኳር ማቆየት፡-** **የተለያዩ ፍራፍሬዎን በስኳር ሳይበላሹ ማቆየት እንችላለን። ለምሳሌ ማንጎ፣አቮካዶ፣ፓፓዬ እና አፕል**

3. **በፀሐይ ማቆየት፡-** **በንፁህ ጨርቅ በታትኖ በማስጣት የማድረቅ ሂደት ነው። ለምሳሌ ስጋ፣ ቲማቲም ፣ ሽንኩርት ፣ ድንች፣ ወይን፣ አተር ፣ ባቄላ፣ ስንዴ ፣ በቆሎ**

4. **በኮምጣጤ ማቆየት፡-** **ምግብን ኮምጣጤ(ቪኔጋር) በመጠቀም ማቆየት እንችላለን። ለምሳሌ ሽንኩርት ፣ ቲማቲም፣ ጎመን ፣ ቃሪያ፣ ሰላጣ፣ ካሮት፣ ዱባ እና ቀይ ስር**

5. **በጭስ ማቆየት፡-** **ምግብን ከእንጨት በሚወጣ ጭስ በመጠቀም ማድረቅ ይቻላል። ለምሳሌ ስጋ እና አሳ**

መልመጃ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ

1. **የመጸዳጃ ቤት ጥቅም ግለፁ።**

2. **የመጸዳጃ ቤት ንፅህና ጉድለት የሚያስከትለው ጉዳት አብራሩ።**

3. **ምግብ ሳይበላሹ ለረዥም ጊዜ ከምናቆይበት ዘዴዎች 3 ት ጥቀሱ።**